# በካልጋሪ የተቃውሞ ሰልፍ

የካልጋሪ ፖሊስ አገልግሎት የሁሉንም ሰው የመናገር ነጻነትና ሰላማዊ ስብሰባ የቻርተር መብቶችን እውቅና ይሰጣል ። በተጨማሪም ነዋሪዎች ፣ ጎብኚዎች እና የንግድ ድርጅቶች ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ የማግኘት መብትዎን  እንገነዘባለን ።

**እኛ ምንቆጣጠረው ባህሪ ን እንጂ እምነትን አይደለም ።**

ተቃውሞ እና ሰልፎችን በሚመለከት ያሉትን ህጎች እና ደንቦት ዝርዝር ለማግኘት Calgarypolice.ca ን ይጎብኙ።

## ከመሄድዎ በፊት:

- ህጎችን እና ደንቦችን ይወቁ

  የካናዳ የመብት እና የነፃነት ቻርተር ፣ ክፍል 2 ፣ እርስዎ የመረጡትን የማመን:አመለካከትዎን እና እሴቶዎን የመግለጽ መብቶን ያረጋግጣል ። ነገር ግን ከለላ የሚያገኙት ሰላማዊ ስብሰባዎች ብቻ ናቸው:በቻርተሩ የሚጠበቁት ሁሉም መብቶች ለምክንያታዊ ገደቦች ተገዢ ናቸው ። መብቶች ሁሉ ፍጹም አይደሉም ።
- መብቶዎን እና ኃላፊነቶዎን ይወቁ
- የፖሊስ ሚና ምን እንደሆነ ይወቁ
- ድርጊቶዎን ከግምት ውስጥ አስገቡ
- ከፖሊስ ጋር ይገናኙ፤ ጥያቄዎን ይጠይቁ

CALGARY POLICE SERVICE

## ማንን ያነጋግሩ

የካልጋሪ ፖሊስ አገልግሎት የፖሊስ ግንኙነት ቡድን (PLT) ሰላማዊ ዝግጅቶችን ለማመቻቸት ከግለሰቦች ወይም ከቡድኖች ጋር ይሠራል ። የግንኙነት መኮንኖች ዝግጅት ለሚያዘጋጁ ወይም ለሚያደራጁ ወይም ዝግጅት ላይ ለመገኘት ለሚያስቡ መረጃ በመስጠት የሚያገለግሉ ናቸው ።

የፖሊስ ግንኙነት ቡድንን ለማግኘት በኢሜል PLT@**calgarypolice.ca.**

QR CODE በ **calgarypolice.ca** ላይ ለተቃውሞ ገጽ ላይ የሚለቀቅ  ።

## ማድረግ የሚችሉት:

- መብቶዎን ለማስከበር በሰላማዊ ሁኔታ መሰብሰብ
- ሀሳብዎን ፣ እምነትዎን እና አስተያየቶን መግለፅ
- መልዕክቶን በህጋዊ መንገድ ማስተላልፍ
- የመደራጀት ነፃነት

## ማድረግ የማይችሉት:

- አውራ ጎዳና መንገድ መዝጋትም ሆነ ማደናቀፍ
- ረብሻ መቀስቀስ ወይም ሁከት ውስጥ መሳተፍ
- በሕገ-ወጥ ስብሰባ ወቅት ወይም የወንጀል ድርጊት ለመፈፀም በማሰብ የተሰወረ አለባበስ መልበስ እና ማድረግ
- የፍርድ ቤት ትዕዛዝን አለመቀበል
- ማንኛውንም ሰው መጉዳት
- እንደ አስለቃሽ ጋዝ ያሉ ንጥረ ነገሮችን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት
- የግል ይዞታን መተላለፍ
- ሰልፍን ማደናቀፍ

## ማድረግ ያለብዎት :

- በግል ይዞታው ባለቤት ወይም በወኪሉ ይዞታውን እንዲለቁ ከተጠየቁ ወዲያውኑ ለቀው መሄድ ። የግል ይዞታን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ካልሆኑ በህገወጥ ድርጊት በቁጥጥር ስር ሲውሉ እና በወንጀል ሊከሰሱ ይችላሉ ።
- በሰላም መኮንን ከታሰሩ የግል መረጃዎን ያቅርቡ ። መረጃዎን ለመስጠት ሕግ ያስገድዳል፤ ይህን አለማድረግ የወንጀል ክስ ሊያስከትል ይችላል ።

## የፖሊስ ሚና

**የካልጋሪ ፖሊስ አገልግሎት:**

- ሰላምን እና የህዝብ ደህንነት መጠበቅ
- በአንድ ክስተት ጉዳት ከደረሰባቸው ጋር መስራት
- የትራፊክ መሰናክሎች በሚከሰቱበት ጊዜ በጉዞ ላይ ያለውን ተፅእኖ ለመቀነስ እና የትራፊክ ፍሰቱን ወደ ቀድሞ ለመመለስ መስራት
- ከግል ባለንብረቶች ጋር በመሆን ይዞታውን እንዲለቁ የተጠየቁ ሰዎች ይዞታውን ለቀው እንዲሄዱ ለማድረግ አብሮ መስራት
- የወንጀል ድርጊትን መመርመር
- በተገቢው መንገድ ለህገ-ወጥ ክስተቶች ምላሽ መስጠት ። አመጽ እና የወንጀል ድርጊትን አይታገስም ።

## እርምጃዎን ያመዛዝኑ

**በህገ ወጥ መንገድ መቃወም የወደፊት ሕይወትዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል ። የወንጀል መዝገብን የሚያስከትሉ ክሶች የሚከተሉትን ሊያስከትሉ ይችላሉ:**

- የጉዞ ገደቦች
- ውስን የሥራ ዕድል
- የመድህን ዋስትና ሲፈልጉ ወይም የመኖሪያ ቤት ሲከራዩ የሚኖረው ተፅዕኖ
- በገንዘብ መቀጮ ክፍያዎች ምክንያት የገንዘብ ችግር
- የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከተጣሰ ተጨማሪ የህግ ጥያቄን ያስከትላል